# የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

## የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ መተዳደሪያ ደንብ አጠቃላይ ትንተና

በባለፈው ጽሁፍ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መተዳደሪያ ደንብ ቅጽ ለ በሙሉ እና ሐ የተወሰኑትን የዳሰስን ሲሆን በዚህ ጽሑፍ ከቅጽ ሐ የቀሩትን በዝርዝር ለመዳደስ እንሞክራልን።

### <u>የማንቀሳቀስ ገደብ</u>

ሌላው በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መተዳደሪያ ደንብ ቅጽ ሐ የተመለከተው የተመዘገቡ ኩባንያዎች ውስጥ ድርሻ ያላቸው ወሳኝ ኢንቨስተሮች አክሲዮን የማንቀሳቀስ ገደብ ነው። እነዚህ ሁለቱምቦርዶችውስጥ ድርሻ ያላቸው ወሳኝ ኢንቨስተሮች አደራጆች፣ ዳይሬክተሮች እና ዋና ኢንቨስተሮች ሲሆኑ ድርሻቸውን የማንቀሳቀስ ገደብ የተጣለባቸው ናቸው። እነዚህ ወገኖች ለዋናው ቦርድ ወይም ለአዳጊ ቦርድ ከተመዘገቡ በኋላ ባሉት አስራ ሁለት ወራት ውስጥ የይዞታቸውን መጠን ከ50% በላይ እንዳይቀንሱ ይገደባሉ። ይህመስፈርት የኩባንያው አደራጆች እና ከፍተኛ ባለድርሻዎች ኩባንያው ከተመዘገበ በኋላ ለኩባንያው ስኬት ቁርጠኛ መሆናቸውን እና ከአዲሶቹ ባለድርሻዎች ጋራ ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ይረዳል። በዚህ የማንቀሳቀስ ገደብ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ አካላት ድርሻቸውን ለሌላ ወገን ማስተላለፍ፣ ማበደር፣ማስያዝ እንደማይችሉ ተገልፆላቸው ቃል መግባት እና ስምምነት መፈረም አለባቸው።

### <u>አባሪ የአክሲዮን ምዝገባ መስፈርቶች</u>

ሌላው በቅጽ ሐ የተመለከተው አባሪ የአክሲዮን ምዝገባ መስፈርት ነው። ይህም አስቀድመው በተመዘገቡ ኩባንያዎች የወጡ ተጨማሪ የድርሻ ሰነዶችን የሚመለከት ነው። ደንቡ አክሲዮን የመግዛት ቅድሚያ መብትን፣የጉርሻ አክሲዮን የማውጣት ጉዳዮችን፣ አክሲዮንን መሰረት ባደረጉ ክፍያዎች፣ በአክሲዮን ላይ የተመሰረቱ ክፍያዎችን፣ በውህደት እና መዋጥ የተመለከቱ የተለያዩ ዘዴዎችን ይደነግጋል። ለእያንዳንዱ ዘዴ የተወሰኑ መስፈርቶች ኩባንያዎች ተጨማሪ ካፒታል ሲያወጡ ወይም እንደገና ሲዋቀሩ ተገቢውን መረጃ እና ጥበቃ እንዲያገኙ ያረጋግጣሉ።

የአክሲዮን ድርሻቸውን አስቀድመው ያስመዘገቡ አውጪዎች በተወሰነ ጊዜ ተጨማሪ አክሲዮኖችን በገበያው እንዲመዘገብ ሊፈልጉ ይችላሉ። ገበያው አውጪዎች አባሪ አክሲኖችን ማስመዝገብ እንዲችሉ በርካታ ዘዴዎችን ያቀርባል። ከእነዚህ ዘዴዎች ውስጥ ለግዢ ቃልኪዳን ማቅረብ፣ ለሽያጭ በማቅረብ፣ አክሲዮኖችን የመግዛት ቅድሚያ መብት፣ የጉርሻ አክሲዮን በማውጣት፣ አክስዮንን መሰረት ባደረጉ ክፍያዎች፣ በውህደት እና መዋጥ፣ ተለዋጭ ሰነዶች እና ገበያው በየጊዜው በሚያፀድቃቸው ሌሎች ማናቸውም ዘዴዎች ሊተገበሩ ይችላሉ።

በመጀመሪያ አውጪዎች ጠቅላላ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። እነዚህም የገበያውን ደንቦች (በተለይም ደንብ 4.4)፣ የካፒታል ገበያ አዋጅ፣የንግድ ህጉን፣የባለስልጣኑን መመሪያዎች እና ሌሎች ተዛማጅ የኩባንያ ህጎችን በጥብቅ ማክበርን ያካትታሉ።

የአባሪ አክሲዮኖች ምዝገባ ማመልከቻዎች ሁሉም አስፈላጊ ሰነዶች እና መረጃዎች ሙሉ በሙሉ ሲቀርቡ ብቻ ተቀባይነት እንዳላቸው ይቆጠራሉ። እንዲሁም አውጪዎች ለዚሁ አላማ ሲባል በገበያው የወጡ የመስፈርቶች መሟላት ማረጋገጫ ሰነድ ዝርዝር ማሟላት እና በጊዜ ሂደት ሊጨመሩ የሚችሉ ተጨማሪ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው።
ከእነዚህ አጠቃላይ ግዴታዎች በተጨማሪ፣ እንደ አክሲዮን አወጣጥ ዘዴው የተወሰኑ መስፈርቶች አሉ።

ለምሳሌ አክሲዮኖችን የመግዛት ቅድሚያ መብት ጉዳዮች የወሰድን እንደሆነ አውጪዎች ለነባር ባለ አክሲዮኖች አዲስ አክሲዮን ሽያጭ ከማውጣታቸው እና ከአባሪው ምዝገባ የሚገኘው ጥቅም መቆጠር የሚጀምርበት ቀን ከመቁረጣቸው በፊት በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ የባለአክሲዮኖችን እና የቦርዱን ፈቃድ ማግኘት፣ የባለሥልጣኑን ፈቃድ ለማግኘት፣የገበያውን ፈቃድ ማግኘት እና ኩባንያው የውክልና ሽያጭ ስምምነት ካስፈለገው ይህንኑ እንዲጠናቀቅ ማድረግ አለባቸው።ከዚህ በተጨማሪ ቅድሚያ የመግዛት መብት ዋጋ ከነባር አክሲዮኖች የገበያ ዋጋ መብለጥ አይችልም።

ሌላኛው የአባሪ አክሲዮኖች ምዝገባ ዘዴ የጉርሻ አክሲዮን ማውጣት ሲሆን አውጪዎች በጉርሻ መልክ ለነባር ባለአክሲዮኖች የሰጡትን ድርሻ በአባሪ ፎርም ማስመዝገብ የሚችሉት ከላይ ለቅድሚያ መብት ዘዴ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ነው። በዚህ ዘዴ ተግባራዊነት ወቅት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ገበያው ከአውጪው ተጨማሪ ሰነዶችን እንዲሟሉ መጠየቅ ይችላል።

ሌላኛው አባሪ አክሲዮኖችን በአውጪው የማስመዝገብ ዘዴ በአክሲዮን ላይ የተመሰረቱ ክፍያዎች በመፈጸም ነው። አንዳንድ ጊዜ ኩባንያዎች ለሰራተኞች፣ ለዳይሬክተሮች ወይም ለአገልግሎት ሰጪዎች ክፍያ መፈጸም ወይም ሽልማት መስጠት ሲፈልጉ በጥሬ ገንዘብ ሳይሆን በአክሲዮን ሊያደርጉ ይችላሉ። በዚህ መልኩ የተሰጠ አክሲዮን፣ በአክሲዮን ላይ የተመሠረተ ክፍያ የሚባል ሲሆን አባሪ ተደርጎ በገበያው እንዲመዘገብ አውጪዎች የአክሲዮን አወጣጥ ውሎችን ደንብ እና ሁኔታዎች የሚገልጽ የመጨረሻውን የጸደቀ የእቅድ ሰነድ ማቅረብ፣በባለሥልጣኑ ማስመዝገብ እና ለገበያው የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ማቅረብ አለባቸው።

ሌላኛው አባሪ አክሲዮኖች የማስመዝገብ ዘዴ የሚከናወነው አውጪው ከሌላ ኩባንያ የመዋሃድ ወይም አንዱ ሌላውን ለመቆጣጠር የሚያበቃ ድርሻ ሲገዛ ነው። አውጪው ሲዋሃድ ወይም አውጪው ኩባንያ ሌላውን ኩባንያ ለመቆጣጠር የሚያበቃ ድርሻ ሲገዛ አዲስ አክሲዮኖች ለገዡው ኩባንያ ባለአክሲዮኖች እንደ ስምምነቱ አካል ሊሰጡ ይችላሉ።

## የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ መተዳደሪያ ደንብ አጠቃላይ ትንተና

ውህደቱን የፈጠረው ኩባንያ ማለትም ከውህደቱ በኋላ የሚቀጥለው ኩባንያ( በውህደቱ ያልተዋጠ እና ያልከሰመ) ቀድሞውኑ በገበያው ላይ የተመዘገበ ከሆነ ይሄው ኩባንያ በውህደቱ የተፈጠሩትን አዳዲስ አክሲዮኖች ለማስመዝገብ ማመልከት አለበት።

በውህደቱ የሚቀጥለው አውጪው ኩባንያ በገበያው ያልተመዘገበ ከሆነ ግን ከውህደቱ በፊት ተመዝግቦ በውህደቱ የተዋጠውን ኩባንያ አክሲዮኖች ለመያዝ በመጀመሪያ ከኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ፈቃድ ማግኘት አለበት። በዚህ ሁኔታተመዝግቦ የነበረው ነገር ግን የተዋጠው ኩባንያ አክሲዮኖች ከገበያው ላይ ከምዝገባ ይሰረዛሉ።

## ቀጣይ ግዴታዎች

የደንቡ ቅጽ ሐ ክፍል 3 (ምዕራፍ 8-12) ለተመዘገቡ ኩባንያዎች የሚተገበሩ ቀጣይ መስፈርቶችን እና ግዴታዎችን ያስቀምጣል። እነዚህ ቀጣይ ግዴታዎች ምናልባት ከመጀመሪያው የምዝገባ መስፈርቶች የበለጠ አስፈላጊ ሊሆኑ ከሚችሉባቸው ምክንያቶች አንዱ እና ዋንኛው በኩባንያው ሕይወት ዘመን ውስጥ በአውጪው እና በገበያው መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገዙ በመሆናቸው ነው።

የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪዎች የአክሲዮን ዋጋዎች ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁሉንም ወሳኝነት ያላቸውን መረጃዎች ወዲያውኑ ይፋ ማድረግ አለባቸው። መተዳደሪያ ደንቡ ወዲያውኑ ማሳወቅ የሚያስፈልጋቸው የአክሲዮን ዋጋን የሚወስኑ መረጃዎች ዝርዝር አስቀምጧል። ይህም በቦርድ ዳይሬክቶሬች ላይ የተደረጉ ለውጦችን፣ የፋይናንስ አፈጻጸም ውጤት፣ የትርፍ ክፍፍል መግለጫዎችን፣የካፒታልና ሌሎች ዋና ዋና ለውጦችን እና የፍርድ ቤት ወይም መሰል የሙግት ሂደቶችን ካሉ ያካትታል።

ሌላው የግብይት ገደብ ወቅት ድንጋጌዎች የተመለከተ ሲሆን በዚህ ጊዜ የኩባንያው ውስጥ አዋቂዎች ከላይ የተዘረዘሩ ወሳኝ መረጃዎች ለህዝብ ይፋ ከመውጣታቸው በፊት በተወሰኑ ጊዜያት ውስጥ በኩባንያው አክሲዮኖች እንዳይገበያዩ ይከለክላሉ።

በሌላ አነጋገር በዚህ ጊዜ የኩባንያው ውስጥ አዋቂዎች (እንደ ዳይሬክተሮች ወይም ከፍተኛ ሠራተኞች ያሉ) ሚስጥራዊ መረጃ ሊኖራቸው ስለሚችል የኩባንያውን አክሲዮኖች መገበያየት አይፈቀድላቸውም። ይህ የግብይት ጊዜ ገደብ የሚጀምረው የአንድ የፋይናንስ አመት መዝጊያ ላይ (የግማሽ ወይም ለሙሉ ዓመት ውጤቶች በሚገለጽበት ጊዜ) ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪው ቦርድ በአሳሳቢ ጉዳዮች ለመወያየት ስብሰባ ከጠራበት ወይም አጀንዳ ወረቀት ከተበተነበት 15 የሥራ ቀናት በፊት ይጀምርና ዋጋ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ መረጃዎች ለገበያው ገቢ ከተደረጉ በኋላ ለ24 ሰዓታት ይቆያል።

በገበያው መተዳደሪያ ደንብ በግልጽ እንደተደነገገው ለዚሁ አላማ ሲባል ኩባንያዎች የውስጥ መረጃ አዋቂ ሰራተኞችን እና አመራሮችን ዝርዝር መያዝ እና እነዚህ ሰዎች የኩባንያውን አክሲዮን ግዥ ወይም ሽያጭ መፈጸም የተከለከሉበት የጊዜ ገደብ የሚጀምርበትን ቀን ለገበያው ማሳወቅ አለባቸው።

ይህም ገበያው የሰዎቹን ማንነት በመለየት በተባለው ጊዜ በኩባንያው አክሲዮን ግብይት እንዳይፈጽሙ ክትትል እንዲያደርግ ይረዳዋል። ይህ አሰራር ውስጥ አዋቂዎች ቀድመው በሚደርሳቸው መረጃ በመነገድ ከሌሎች የተሻለ ትርፍ እንዳያገኙ በማድረግ በመረጃ አለመመጣጠን ሊደርስ የሚችልን ጉዳት ያስቀራል። ሌላው ስለ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ አውጪው የኮርፖሬት ሃላፊነት የሚደነግገው ምዕራፍ ሲሆን የአውጪው ኩባንያ ዳይሬክተሮችን ግዴታዎች፣ የቦርድ እና አጠቃላይ ስብሰባዎችን በአግባቡ መደረግ እንደሚገባ ይጠቁማል። ለደንቡ መከበር የአውጪው ኩባንያ ዳይሬክተሮች በጋራ እና በተናጠል ተጠያቂ መሆናቸውን እና የደንቡ መጽሐፍ ቢያንስ ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች የተቀመጡት ደረጃዎች መሠረት የታማኝነት ግዴታዎችን እንዲወጡ ይጠብቅባቸዋል።

ሌላው የተዛማጅ ወገን ግብይቶችን የተመለከተ ሲሆን በተመዘገቡ ኩባንያዎች እና ከእነሱ ጋር በሚዛመዱ ሰዎች መካከል የተደረጉ ግብይቶች በ24 ሰዓታት ውስጥ ይፋ መደረግ አለባቸው።

## ማገድ እና ከምዝገባ መሰረዝ

በዚህ ክፍል ምዕራፍ 11 እና 12 ኩባንያዎችን ግብይትን ማገድ ወይም ሰነዶችን ከምዝገባ መሰረዝ ስለሚቻልባቸው ሁኔታዎች ይደነግጋል። በሌሎች በተለያዩ ምክንያቶች ጨምሮ የደንብ ጥሰቶች ሲፈጸሙ ወይም በባለሥልጣኑ አቅጣጫ መሰረት ገበያው ግብይት በተለያዩ ምክንያቶች ሊያግድ እንደሚችል ተቀምጧል። በአውጪው አመልካችነት የሚደረጉ የግብይት እገዳዎች በተረጋገጡ ምክንያቶች ተደግፈው መቅረብ አለባቸው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ከገበያው ምዝገባ መሰረዝ በፈቃደኝነት (በአውጪው ጥያቄ) ወይም በተቆጣጣሪ (በገበያው) ሊወሰን እንደሚችል ነው።

በተቆጣጣሪው የሚደረግ ስረዛ ህጎችን ባለማክበር፣ በቂ የሆነ ለሕዝብ የቀረበ አክሲዮን ባለመኖር፣ ለረጅም ጊዜ እንቅስቃሴ ባለማድረግ፣ በአውጪው ፈቃድ መሰረዝ ወይም ሌሎች ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል።

በሌላ በኩል የተመዘገበውን ኩባንያ ለመጠቅለል የሚያበቃ አክሲዮን ድርሻ በመግዛት እና ለባለአክሲዮኖች የግዢ ጥያቄ ማቅረብን ጨምሮ ኢንቨስተሮችን ያለ ፍትሃዊ ካሳ ከኢንቨስትመንታቸው እንዳይወጡ ለመከላከል ሲባል በፈቃደኝነት ከምዝገባ መሰረዝ ሊከናወን ይችላል።

## ልዩ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች

የቅጽ ሐ ክፍል 4 እስከ 6 ስለ ልዩ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የምዝገባ መስፈርቶችን በተመለከተ ይደነግጋል። የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ስለሚወጣው ሰነድ መጠን፣ ምዝገባ እና በአንዳንድ ሁኔታዎች የጠባቂ ሹመት የመሳሰሉ የተወሰኑ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። በመንግስት የሚወጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ልዩ ባህሪያት ከግምት ውስጥ በማስገባት ቀለል ያሉ የምዝገባ መስፈርቶች ተቀምጧል።

## በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ ለግብይት የቀረበ ፈንድ

በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ ለግብይት የቀረበ ፈንድ ማለት እንደ አክሲዮኖች፣ ቦንዶች ወይም እቃዎች ያሉ ብዙ የተለያዩ ኢንቨስትመንቶችን በአንድ ቅርጫት የያዘ ነው። ኢንቨስተሮች በግብይት ወቅት የእነዚህን ፈንዶች አክሲዮኖች መግዛት እና መሸጥ ይችላሉ። ፈንዶቹ በስራቸው ምን ምን ንብረቶች እንዳሉ በግልጽ የሚያሳዩ ናቸው። ይህ የተለያዩ ኩባንያዎችን አክሲዮን በአንድ ቋት ከያዘ ፈንድ ላይ አክሲዮን መግዛት ለኪሳራ ተጋላጭነትን ይቀንሳል።

ለምሳሌ "Top 30 Ethiopia Fund" የሚባል ፈንድ የተቋቋመ በኢትዮጵያ የሰነደ ሙኣለ ንዋይ ገበያ ላይ ከተመዘገቡት የ30 ትላልቅ ኩባንያዎችን አክሲዮኖችን የሚይዝ ቢሆን አንድ ፈንድ አንድ አክሲዮን በመግዛት፣ ከ30ዎቹ ኩባንያዎች ውስጥ አነስተኛ ክፍሎችን በተዘዋዋሪ መያዝ ይቻላል ማለት ነው። እነዚያ 30 ኩባንያዎች እያንዳንዳቸው በገበያው ተመዝግበው እየተገበያዩ የሚገኙ ስለሚሆኑ ዋጋቸው ቢጨምር የፈንዱ አክሲዮን ዋጋም ይጨምራል።

የአንድ ኩባንያ አክሲዮን እንደ መግዛት ወይም መሸጥ ሁሉ የ30 ኩባንያዎችን አክሲዮን የሚይዘውን ፈንድ በገበያው በቀላሉ በአንድ ግብይት መግዛት ወይም መሸጥ ይችላል። በዚህ መንገድ እያንዳንዱን ኩባንያ አክሲዮን ለብቻው ከመግዛት ይልቅ ሁሉንም በአንድ ቅርጫት ውስጥ የያዘውን የፈንዱን አክሲዮን በመግዛት ሊያገኙ የሚችሉበት ሁኔታ ተመቻችቷል።

አንድ ኩባንያ በገበያው ለግብይት የሚቀርቡ ፈንዶች ለማውጣት ሲፈልግ፣ ለገበያው ግልጽ መረጃ መስጠት አለበት። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፦ የአውጪውን ማንነት፣ ለግብይት የቀረቡ ፈንዶች እንዴት እንደ ተዋቀረ እና በምን ንብረቶች ላይ የተመሠረተ እንደሆነ፣ የፈንዱ የአሁን የተጣራ የንብረት ዋጋ (Net Asset Value)፣ የእያንዳንዳቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች /ኢንዴክስ/ መሠረታዊ ንብረቶች ባለፉት ስድስት (6) ወራት ውስጥ በየሳምንቱ የነበራቸው የተጣራ የንብረት ዋጋ ለውጥ፣ ፈንዱ የተደገፈበት ንብረት የገንዘብ አከል መጠን ዝርዝር ( ጠቅላላ ሽያጭ/ የገበያ ካፒታላይዜሽን) ፣የአስተዳደር ክፍያዎች እንዴት እንደሚሰሉ፣ ፈንዱ የሚዋቀርበት እና የሚገበያይበት የገንዘብ አይነት እና ሌሎች በገበያው የሚጠየቁ መስፈርቶች መሟላት አለባቸው።

በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ላይ ለግብይት የሚቀርቡ ፈንዶች በገበያው ለመመዝገብ በአይነታቸው ክፍት መሆን አለባቸው። ይህ ሲባል ማንኛውም ኢንቨስተር በማንኛውንም ጊዜ ለመቀበል፣ ለማሳተፍ፣ ለመግባት እና ለመውጣት ክፍት እና ቀላል መሆን አለባቸው ማለት ነው። በተጨማሪ ተቀባይነት ባለው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ስብስብ /የገበያሁኔታ አመላካች/ መሰረታዊ ንብረት ጥቅል ላይ ተመስርቶ የወጣ መሆን፣ ሁልጊዜም ቢሆን ሙሉ በሙሉ በፈንዱ ሀብቶች የተሸፈኑ ወይም ሙሉ ዋስትና ያለው እና ተቀባይነት ያገኘ መሆን፣ ፈንዶች የተመሰረቱበት ንብረት የተጣራ የሃብት ዋጋ ለማወቅ የስሌት ዘዴ ያለው፣ የኢንቨስተሮችን ጥቅም ለመጠበቅ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ በጠባቂ የተያዙ እና ዕለታዊ ዋጋዎችን ለማቅረብ በወሰኑ የገበያ ከፋቾች የተደገፉ መሆን አለባቸው።

## የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ መተዳደሪያ ደንብ አጠቃላይ ትንተና

በተጨማሪም የሚመለከተው የስር የገበያ ሁኔታ አመላካች (underlying Index) ወይም ፖርትፎሊዮ በገበያው ላይ የተመዘገቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ያካተተ መሆን፣ በገበያው የተመዘገበ ፈንድ ለማስተዳደር የሚያስችል እውቀት (ወይም እውቀት የማግኘት እድል) ያለው መሆኑን ማሳየት፣ኢንቨስተሮች ፈንዱን መገበያየት እንዲችሉ ሁለተኛ ደረጃ ገበያ መኖሩን ማረጋገጥ፣ እና የፈንዱን የተጣራ የንብረት ዋጋ በየቀኑ ለማስላት እና ለሁሉም የገበያ ተዋንያን በተመሳሳይ ጊዜ ይፋ ለማድረግ ቃል መግባት አለበት። በመጨረሻም እንደ ትርፍ ክፍፍል ያሉ ገቢዎችን በተመለከተ ቢያንስ በየአመቱ እና የሽያጭ ሰነዱ ላይ ከተቀመጥው ጊዜ በፊት ለኢንቨስተሮች መከፋፈል አለበት።
እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ ፈንዶችን ለማውጣት እና በገበያው ለመመዝገብ የሚያበቁ መስፈርቶች በገበያው መተዳደሪያ ደንብ ከላይ በተገለጸው መልኩ ተዘርዝሮ ይገኛሉ።
በቀጣይ ከኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ መተዳደሪያ ደንብ ቅጽ መ እና ሠን በጥልቀት የምንዳስስ ይሆናል።